


# አሁንስ ምን አስበሻል ኤርትራ?

አወይ ኤርትራ መከራሽ መብዛቱ!
ጠላትን ከወዳጅ አቅቶሽ መለየቱ፤
ኢትዮጵያን ወረርሽ ገና በጠዋቱ፤
እሳት አቀጣጥለሽ ገባሽ ከመዓቱ፤
የማይደርስ የለም ደረሰ ሰዓቱ፤
ድንበር ጠባቂዎቹ በቃ ተሰናበቱ።

ድንበርሽ ጠብቀው በሰላም ባቆዩ፤
ገብስን ከእንክርዳድ አጣርቶው በለዩ፤
ግፍ ደረሰባቸው ፍዳቸውን አዩ፤
በጥም በረሀብ በጣም ተሰቃዩ።

የበረሃው ኑሮ ምንም ሳይበግራቸው፤
ሰላምን ለማስፈን ከልብ ቃል ገብተው፤
ተልእኮን ማሳካት ነበር አላማቸው።

በእጅ ላይ ያለ ወርቅ፤
በጣምም ቢያምር እጅግም ቢደምቅ፤
ከእጅ እስከሚያመልጥ ከእይታ እስከሚርቅ፤
መልካም አገልግሎቱ በውኑ አይታወቅ

ሆነ እና ነገሩ የሰላም አስከባሪዎቹ ነገር፤
አበሳቸውን አይተው በማያውቁት አገር፡
ተሰናብተው ወጡ ያለአንዳች ቁምነገር።

ገና ከልጅነት ለትዳር ቸኩለሽ፤
ምንም ሳይኖርሽ እናት እሆናለሁ ብለሽ፤
በባዶ ተስፋ ብዙ ተኩራርተሽ፤
አወይ ኤርትራ እጅግም ተታለልሽ!
ይሻልሽ ነበረ መኖር ከእናትሽ፤
ልጆችሽ ተጎዱ አንችም አልተመቸሽ።

ኢሳያስ ነው መሪሽ አንድና ደንቆሮ፤
ምንም የማይገባው የዜጎችን እረሮ፤
ምን ይውጠው ይሆን ጠባቂዎቹን አባ'ሮ?

ሰላም አስከባሪዎችን አባረሽ ከአስመራ፤
የሚቃኝ ቢጠፋ ያንን ሽሎቀና ተራራ፤
አሁንስ ምን አስበሻል አገረ-ኤርትራ?

መዝገበ ገብረክርስቶስ